በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ቤተ ክርስቲያን - ክፍል 3


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** **ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**

**በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ**12፡30 – 1፡30

**ኅዳር ፳ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

## *የአይሁድ ተቃውሞ*

- **"የሚያምኑትም ከፊት ይልቅ ለጌታ ይጨምሩለት ነበር።"** ***የሐዋ. ሥራ. 5፡14***

(ሀ) <u>በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተክስቲያን</u>

- ቤተ ክርስቲያን የተወለደችው በበዓለ ሃምሳ በኢየሩሳሌም ነው። ከበዓለ ሃምሳ በኋላም በክርስቶስ ያመኑት ወደየሀገራቸው ተመልሰው ክርስትናን አስፋፉ። ***የሐ. ሥራ 2፡1-...***

- የእግዚአብሔር መንፈስ በሐዋርያት ይሠራ ነበርና የአማኞች ቁጥር በየቀኑ ይጨምር ነበር። በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ብቻ ከ3,000 እስከ 5,000 ደረሰ። "ነገር ግን ቃሉን ከሰሙት ብዙዎች አመኑ። የወንዶችም ቁጥር አምስት ሺህ ያህል ሆነ።" ***የሐዋ.ሥ. 4፡4***

- በቀጣይነት የመብዛታቸው ምክንያትም፡-የሚፈጸሙ ተአምራት እና በፍቅርና በጽድቅ የተሞላው የክርስቲያኖች ሕይወት ነበር። "ሕዝቡ ግን ያከብሩዋቸው ነበር። የሚያምኑትም ከፊት ይልቅ ለጌታ ይጨመሩለት ነበር።" ***የሐዋ.ሥ. 5፣14፣ የሐዋ.ሥ. 6 እና 7።*** "እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝቡ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።" ***የሐዋ. ሥ 2፡47።***

- በዚህ ምክንያትም አይሁድ በቅናት በክርስቲያኖች ላይ ተነሱ።

# <u>ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት</u>

***<u>ክርስቲያኖች ከአይሁድ የደረሠባቸው እንግልት</u>***:-

- አይሁድ በክርስቶስ፣በሐዋርያት እና በክርስቲያኖች ላይ የነበራቸውን ተቃውሞ ወንጌል በግልጥ አሳይቶናል።

- ሰዎች ክርስቶስን ሲከተሉ ሲያዩ አይሁድ በቅናት ተነሳስተው "ግደለው፣ ስቀለው" ይሉ ነበር።"የካህናት አለቆችና ሽማግሎች ግን በርባንን እንዲለምኑ ኢየሱስን ግን እንዲያጠፉ ሕዝቡን አባበሉ::" ***<u>ማቴ. 27:20።</u>***

- ቅዱስ እስጢፋኖስን ጠልተው በድንጋይ ሲወግሩትም "የነጻ ወጪዎች ከተባለችው ምኩራብም ከቀሬናና ከእስክንድርያም ሰዎች ከኪልቅያና ከእስያም ከነበሩት አንዳንዶቹ ተነሥተው እስጢፋኖስን ይከራከሩት ነበር፤ይናገርበት የነበረውንም ጥበብና መንፈስ ይቃወሙ ዘንድ አልቻሉም:: በዚያን ጊዜ:- በሙሴ ላይ በእግዚአብሔርም ላይ የስድብን ነገር ሲናገር ሰምተነዋል የሚሉ ሰዎችን አስነሡ:: ሕዝቡንና ሽማግሌዎችንም ጻፎችንም አናደዱ፤ቀርበውም ያዙት፤ወደ ሸንጎም አመጡትና:-ይህ ሰው በዚህ በተቀደሰው ሥፍራ በሕግም ላይ የስድብን ነገር ለመናገር አይተውም፤ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ይህን ስፍራ ያፈርሰዋል፤ሙሴም ያስተላለፈልንን ሥርዓት ይለውጣል ሲል ሰምተነዋልና የሚሉ የሐሰት ምስክሮችን አቆሙ::" ***<u>የሐዋ. ሥ. 6:9-14 ።</u>***

- በቅዱስ ጳውሎስ ላይ ያደረጉትንም ተቃውሞ በሐዋርያት ሥራ ላይ በተለያዩ ክፍሎች እናነባለን:: "ብዙ ቀንም ሲሞላ አይሁድ ሊገድሉት ተማከሩ፤ሳውል ግን አሳባቸውን አወቀ:: ይገድሉትም ዘንድ በሌሊትና በቀን የከተማይቱን በር ሁሉ ይጠብቁ ነበር።" ***<u>የሐዋ.ሥ. 9፣23-25።</u>***
- "አይሁድ ግን የሚያመልኩትን የከበሩትንም ሴቶችና የከተማውን መኳንንት አወኩ፤በጳውሎስና በበርናባስም ላይ ስደትን አስነሥተው ከአገራቸው አወጡአቸው::" ***<u>የሐዋ.ሥ 13:50 ።</u>*** "ወደ ኢያሶን ቤት ቀረቡ፤ባላገኙአቸውም ጊዜ ኢያሶንንና ከወንድሞች አንዳንዶችን ወደ ከተማው አለቆች ጎትተው:- ዓለምን ያወኩ እነዚህ ወደዚህ ደግሞ መጥተዋል:: ኢያሶንም ተቀብሏቸዋል፤እነዚህም ሁሉ:- ኢየሱስ የሚሉት ሌላ ንጉሥ አለ እያሉ የቄሣርን ትእዛዝ ይቃወማሉ ብለው ጮኹ:: ሕዝቡና የከተማውም አለቆች ይህን ነገር በሰሙ ጊዜ ታወኩ::" ***<u>የሐዋ. ሥ. 17:6-8።</u>***

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

**ክርስቲያኖች ከአይሁድ የደረሠባቸው እንግልት**፡-

- “የከተማውም ሕዝብ ተከፍለው እኩሌቶቹ ከአይሁድ እኩሌቶቹም ከሐዋርያት ጋር ሆኑ፡፡ አሕዛብና አይሁድ ግን ከአለቆቻቸው ጋር ሊያንገላቱአቸውና ሊወግሩአቸው ባሰቡ ግዜ፤አውቀው ልስጥራንና ደርቤን ወደሚባሉት ወደ ሊቃኦንያ ከተማዎች በእነርሱም ዙሪያ ወዳለው አገር ሸሹ፡፡” ***የሐ. ሥ 14፡4-6፡፡*** “ይህንም ብለው እንዳይሠውላቸው ሕዝቡን በጭንቅ አስተውአቸው፡፡ አይሁድ ግን ከአንጾኪያና ከኢቆንዮን መጡ፤ሕዝቡንም አባብለው ጳውሎስን ወገሩ የሞተም መስሎአቸው ከከተማ ወደ ውጭ ጎተቱት፡፡” ***የሐዋ.ሥ.14፣18-19፡፡***
- ቅዱስ ጳውሎስም ከአይሁድ ብዙ መከራ እንደተቀበለ እንዲህ ሲል ገልጾልናል፡-“እነዚያም ጌታን ኢየሱስን ደግሞ ገደሉ ነቢያትንም እኛንም አሳደዱ፤እግዚአብሔርንም ደስ አያሰኙም፤ሰዎችንም ሁሉ ይቃወማሉ፤ ሁልጊዜ ኃጢኣታቸውን ይፈጽሙ ዘንድ አሕዛብ እንዲድኑ እንዳንናገራቸው ይከለክሉናልና፡፡ነገር ግን ቁጣው ወደ እነርሱ ፈጽሞ ደርሶአል፡፡” ***1ኛ ተሰ. 2፡15-16፡፡***
- ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም ከሐዋርያት ቀድሞ በሰማዕትነት አርፎአል፡፡ “በዚያን ዘመን ንጉሡ ሄሮድስ መከራ ያጸናባቸው ዘንድ ከቤተ-ክርስቲያኑ በአንዳንዶቹ ላይ እጁን ጫነባቸው፡፡ የዮሐንስንም ወንድም ያዕቆብን በሰይፍ ገደለው፡፡” ***የሐዋ. ሥ.12 1-2፡፡***
- ከዚያም ቅዱስ ጴጥሮስ ታሠረ፡፡ ***በሐዋ. ሥ. 12፡፡***

**የመከራው ፍሬዎች**

- ስደቱ እስከተነሳበት ጊዜ ሐዋርያት በሙሉ ኃይላቸው ተሰባስበው ያስተማሩት በኢየሩሳሌም ነበር፡፡ከዚያም ከኢየሩሳሌም የተሠደዱ ክርስቲያኖች በተለያዩ ከተሞች የእግዚአብሔርን ቃል አደረሱ፡፡ “የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ፡፡” ***የሐዋ.ሥ. 8፡4፡፡***
- ቅዱስ ጳውሎስም “ይህንም ደግሞ በኢየሩሳሌም አደረግሁት ከካህናት አለቆችም ሥልጣን ተቀብዬ እኔ ከቅዱሳን ብዙዎችን በወኅኒ አሳሰርኋቸው፤ሲገድሉአቸውም አብሬ ተቸሁ፡፡ በምኩራብም ሁሉ ብዙ ጊዜ እየቀጣሁ ይሰድቡት ዘንድ ግድ አልኋቸው ያለ ልክ ስቈጣባቸውም እስከውጭ አገር ከተማዎች ድረስ እንኩዋ አሳድድ ነበር፡፡” ***የሐዋ.ሥ. 26፣10-11፡፡*** ብሎአል፡፡
- መከራና ስደቱም ቃለ ወንጌል በተለያዩ ከተሞች እንዲዳረስና ክርስትና ከጥንካሬ ጋር እንዲስፋፋ አደረገ፡፡

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

## ስብከተ ወንጌል በሰማርያ

- ሰማርያ ሙሉ በሙሉ ጣዖት የሚመለክባት አልነበረችም፡፡ስለ ሰማርያ ***በ2ኛ ነገሥት. 17፣24-34*** አንብቡ፡፡ ክርስትና በሰማርያ ከተሞች መሰበክ ነበረበት፡፡ ይህም በሐዋርያት እና ሰማርያውያንን ይጠሉ በነበሩበት አይሁድ ዘንድ ጠላትነትን ለረጅም ጊዜ እንዲሆን አደረገ፡፡
- መጀመሪያ ወንጌልን በሰማርያ ከተሞች የሰበከው ከሰባቱ ዲቆናት አንዱ የሆነው ፊልጶስ ነው፡፡ጌታችንም በብዙ ተአምራት አገልግሎታቸውን ያጸና ነበር፡፡ “ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው፡፡ ሕዝቡም የፊልጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ ያደርጋት የነበረውንም ምልክት ባዩ ጊዜ፤የተናገረውን በአንድ ልብ አደመጡ፡፡ ርኩሳን መናፍስት በታላቅ ድምጽ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡ ነበርና ብዙም ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ፤በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ፡፡” ***የሐዋ. 8፡5-8፡፡***
- ከዚያም ቅዱስ ጴጥሮስ እና ቅዱስ ዮሐንስ በሰማርያ አስተማሩ “በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበሉ ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው፡፡ እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው በጌታ በኢየሱስ ስም ብቻ ተጠምቀው ነበር እንጂ ከእነርሱ በአንዱ ላይ ስንኩዋ ገና አልወረደም ነበርና፡፡ በዚያን ጊዜ እጃቸውን ጫኑባቸው መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ፡፡” ***የሐዋ. ሥ. 8፡15-17*** “እነርሱም ከመሰከሩና የጌታን ቃል ከተናገሩ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ በሳምራውያን በብዙ መንደሮችም ወንጌልን ሰበኩ፡፡” ***የሐዋ.ሥ. 8፡25***
- ክርስቶስ ለኢትዮጵያዊው የተሰበከበትን ታሪክም ***የሐዋ.ሥ. 8፡26-40*** እናንብብ፡፡

## ክርስቶስ በባሕር ዳርቻዎች ባሉ ከተሞችም ተሰበከ

- ፊልጶስ ወደ ፍልስጤም ከተሞችና በባሕር ዳርቻዎች ሄዶ አስተማረ፡፡ “ከውኃውም ከወጡ በኋላ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም፤ ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ ነበርና፡፡ ፊልጶስ ግን በአዛጦን ተገኘ፤ ወደ ቂሣርያም እስኪመጣ ድረስ እየዞረ በከተማዎች ሁሉ ወንጌልን ይሰብክ ነበር፡፡” ***የሐዋ.ሥ 8፣39-40፡፡***

# <u>ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት</u>

<u>ስብከተ ወንጌል በገሊላ</u>

- ክርስትና በገሊላ ቀድሞ ተሰበኮ ነበር፡፡ “በይሁዳም ሁሉና በገሊላ በሰማርያም የነበሩት አብያተ-ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ ታነጹም፤ በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስቅዱስ መጽናናት እየሄዱ ይበዙ ነበር፡፡” ***<u>የሐዋ.ሥ. 9:31፡፡</u>***
- ቅዱስ ጳውሎስ በ37 ዓ.ም ክርስቲያን ሆነ፡፡ ***<u>የሐዋ. ሥ. 9:1-6</u>*** እናንብብ፡፡

*<u>ምን ተማርን</u>*

- የክርስቶስ ብርሃን የዲያብሎስን ጨለማ አጥፍቶአል፡፡ ለዚህም ነው ክርስትና የሚቃወሙትን ኃይሎች በሙሉ አሸንፎ በዓለም የተስፋፋው፡፡
- በተመሳሳይም የኃጢአትን ጨለማ ለማጥፋት ከፈለግን የክርስቶስ ብርሃን በልባችን አንጸባርቆ የኃጢአት ጨለማ ሊርቅ ይገባል፡፡

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

(ለ) <u>ከኢየሩሳሌም ውጪ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን</u>

- ቤተ ክርስቲያን በቅድሚያ የተመሠረተችው በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳ፣ በገሊላ፣ በሰማርያና በሜዴትራንያን ባሕር በሚገኙ ጥቂት ከተሞች ነበር፡፡ አዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን በነዚህ ሥፍራዎች ተወስና የቆየችው ለአሥራ ሁለት ዓመታት ያህል ብቻ ነበር፡፡
- በመቀጠልም ክርስትና ከኢየሩሳሌም ውጪ በሚገኙ ሌሎች የዓለም ክፍሎች ተስፋፋ፡፡ ከኢየሩሳሌም ውጪም በደማስቆና በአንጾኪያም ታላላቅ የክርስቲያኖች ማህበራት ተስፋፉ፡፡

***<u>በደማስቆ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን</u>***

- ከኢየሩሳሌም ውጪ የነበረችው የመጀመሪያዋ የክርስቲያኖች ማዕከል ደማስቆ ነበረች፡፡
- ቤተ ክርስቲያኒቱ ሳውል በ37 ዓ.ም. ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት የተመሠረተች ናት፡፡ *<u>በሐ.ሥራ 9፡1-9 ፡፡</u>* እንደተጻፈው ሳውል ክርስቲያኖችን ሊያሳድድ ከኢየሩሳሌም ወደ ደማስቆ ይሄድ ነበር፡፡

***<u>በአንጾኪያ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን</u>***

- አንጾኪያ በሕንጻዎችዋና በሥነ ምድራዊ አቀማመጥዋ የታወቀች ከተማ ነበረች፡፡
- ከሮምና ከእስክንድርያ ቀጥሎ የምትገኝ ሦስተኛዋ ታላቅ የሮማ መንግሥት ከተማ ነበረች፡፡
- በቅዱስ እስጢፋኖስ ሞት የተነሳ በተበተኑት ደቀመዛሙርት አማካይነት የተሰበከት ከተማ ነበረች፡፡

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

- “በእስጢፋኖስም ላይ በተደረገው መከራ የተበተኑት እስከ ፊንቄ እስከ ቆጵሮስም እስከ አንጾኪያም ድረስ ዞሩ፥ ቃሉንም ለአይሁድ ብቻ እንጂ ለአንድ ስንኳ አይናገሩም ነበር። ከእነርሱ ግን የቆጵሮስና የቀሬና ሰዎች የነበሩት አንዳንዶቹ ወደ አንጾኪያ መጥተው የጌታን የኢየሱስን ወንጌል እየሰበኩ ለግሪክ ሰዎች ተናገሩ። የጌታም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረ፤ ቍጥራቸውም እጅግ የሚሆን ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ዘወር አሉ።” ***የሐ. ሥራ 11፡19-21።***
- ጣዖትን ያመልኩ ከነበሩት ግሪካውያን ብዙዎቹ ክርስቲያኖች ሆኑ።
- አንጾኪያ ክርስቲያኖች የሆኑ አሕዛብ የመጀመሪያዋ ማዕከል ነበረች።
- የክርስቲያን ማኅበርን በአንጾኪያ በተቋቋመበት ወቅት በኢየሩሳሌም የሚገኙ ሐዋርያት በርናባስን ወደ አንጾኪያ ልከው ነበር። በርናባስም በጣም ውጤታማ የሆነ አገልግሎትን ፈጽሞ ነበር። “ወሬውም በኢየሩሳሌም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ስለ እነርሱ ተሰማ፥ በርናባስንም ወደ አንጾኪያ ላኩት።” ***የሐ. ሥራ 11፡22።***
- ሳውል (ቅዱስ ጳውሎስም) በአንጾኪያ ከበርናባስ ጋር ከተገናኘ በኋላ በአንጾኪያ አንድ ዓመት አብረው አገልግለዋል። “ባገኘውም ጊዜ ወደ አንጾኪያ አመጣው። በቤተ ክርስቲያንም አንድ ዓመት ሙሉ ተሰበሰቡ፥ ብዙ ሕዝብንም አስተማሩ፤ ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ።” ***የሐ. ሥራ 11፡26***

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

- በአንጾኪያ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን እንደ ተመሠረተች ብዙ የመንፈስቅዱስን ፍሬ፣ ብዙ ብቃትም የነበራቸው ተከታዮችን አፍርታ ነበር። "በአንጾኪያም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ፤ እነርሱም በርናባስ፥ ኔጌር የተባለው ስምዖንም፥ የቀሬናው ሉክዮስም፥ የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄሮድስም ባለምዋል ምናሔ፥ ሳውልም ነበሩ። እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ። በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ። በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው።" *__የሐ. ሥራ 13፡1-3።__*
- በአንጾኪያ የነበሩ ክርስቲያኖችም ከአይሁድ ተጽእኖ ሙሉ ለሙሉ ነጻ ነበሩ፤ ክርስቲያን ተብለውም በመጠራት የሁሉም መጠሪያ ለሆነው ስም ቀዳሚ ሆነዋል። "ባገኘውም ጊዜ ወደ አንጾኪያ አመጣው። በቤተ ክርስቲያንም አንድ ዓመት ሙሉ ተሰበሰቡ፥ ብዙ ሕዝብንም አስተማሩ፤ ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ።" *__የሐ. ሥራ 11፡26።__*

*__(ሐ) የ70 ዓ.ም. የኢየሩሳሌም ወድመትና የቤተመቅደሱ መፍረስ__*

- በኢየሩሳሌም በቤተመቅደሱ ከአይሁድ የሚሰበሰብ ብዙ ገንዘብ ተከማችቶ ነበር። ጌታችንም ይከፍል እንደነበር *"ነገር ግን እንዳናሰናክላቸው፥ ወደ ባሕር ሂድና መቃጥን ጣል፥ መጀመሪያም የሚወጣውን ዓሣ ውሰድና አፉን ስትከፍት እስታቴር ታገኛለህ፤ ያን ወስደህ ስለ እኔና ስለ አንተ ስጣቸው አለው።"* *__ማቴ 17፡27።__* በማለት ገልጧል። ማንኛውም መባእ የሚቀርበውም በቤተመቅደስ ብቻ ነበር። የአይሁድ ሕይወታቸውና ተስፋቸው ሁሉ ከቤተ መቅደሱ ጋር የተቆራኘ ነበር። ከኢየሩሳሌም ውጪ የነበሩ ምኩራቦች የጸሎት ሥፍራ ከመሆን ውጪ ምንም ዓይነት መባ የሚሰበሰብባቸው አልነበሩም።

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

## ጌታችን ስለ ቤተ መቅደሱ መፍረስ ተናግሮ ነበር

- "ኢየሱስም ከመቅደስ ወጥቶ ሄደ፥ ደቀ መዛሙርቱም የመቅደሱን ግንቦች ሊያሳዩት ቀረቡ። እርሱ ግን መልሶ፦ ይህን ሁሉ ታያላችሁን? እውነት እላችኋለሁ፥ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም አላቸው።" ***ማቴ 24፡1-2፡፡***

## የኢየሩሳሌም መፍረስ

- ከ64-70 ዓ.ም. ድረስ በሮም የነበረው ቄሳር ኔሮን የጌታችን ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ለስድስት ዓመታት አይሁድን አብዝቶ ያስጨንቃቸው ነበር፡፡
- አይሁድም በምላሹ በሮማ ገዢዎች ላይ አመጽ አስነሱ፡፡ አይሁድ የሮማ ገዢዎችን እየተጋፉ እንደሆነ የሚያስረዳው ይህ ዜናም ሮም ደረሰ፡፡

## የ70 ዓ.ም. ውድመት

- በሚያዚያ 70 ዓ.ም. ሮማውያን ኢየሩሳሌምን አጠቁ፣ በመላ ኢየሩሳሌምም ረሐብ ነገሠ፤ ብዙ ሺዎችም አለቁ፡፡ በመቀጠልም ብዙ ደም ፈሶ ኢየሩሳሌም ሙሉ ለሙሉ ወደመች፡፡
- "እርሱም ከብዙ ሰዎች ጋር ጽኑ ቃል ኪዳን ለአንድ ሱባዔ ያደርጋል በሱባዔውም እኵሌታ መሥዋዕቱንና ቍርባኑን ያስቀራል በርኵሰትም ጫፍ ላይ አጥፊው ይመጣል እስከ ተቈረጠውም ፍጻሜ ድረስ መቅሠፍት በአጥፊው ላይ ይፈስሳል።" ***ዳን 9፡27፡፡*** "እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ፥ አንባቢው ያስተውል፥" ***ማቴ 24፡15፡፡*** የተባለውም ትንቢት ተፈጸመ፡፡

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

## *ከኢየሩሳሌም መውደምና ከቤተ መቅደሱ መፍረስ በኋላ የነበረው የአይሁድ ዕድላቸው*

- አይሁድ እጅግ ደኸዩ ለቤተመቅዱሱ የሚያቀርቡትንም መባ አቋረጡ፡፡

## *የኢየሩሳሌም መውደም በክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን ላይ ያስከተለው ተጽእኖ*

- ጌታችን ስለ ቤተመቅደሱ መውደቅ የተናገረውን ትንቢት በማመን ኢየሩሳሌም ከመውደምዋ አራት ዓመታት በፊት አስቀድመው ክርስቲያኖች ከተማዋን ለቀው ወጥተው ነበር፡፡ “እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ፥ አንባቢው ያስተውል፡፡” ማቴ 24፡15፡፡
- ከ70 ዓ.ም. የኢየሩሳሌም መውደም በኋላ የክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን ዕድገት እጅግ ከፍ ያለ ነበር፡፡
- የአይሁድን ሃይማኖትና ባሕል ይከተሉ የነበሩ ከዚያ ተለይተው ወደ ክርስትና እምነት መጡ፡፡

## *ምን ተማርን?*

- ጌታችን የተናገረው ቃል የሚፈጸም መሆኑን፡፡
- በርካታ የሐሰት ወይም የክህደት ትምህርቶችን ብንሰማም እግዚአብሔር የተናገረው ግን ዘወትር እውነት ነው፡፡
- በርካታ የተሳሳቱ “ሃይማኖቶች” በዓለም ስለሚገኙ ሁሉም ሐሳቦች በጎ፣ ሁሉም ሰዎች ወይም “ሃይማኖቶች” ትክክል ሊሆኑ አለመቻላቸውን፡፡
- እነዚህ የጨለማ ሥራ የሆኑ የተሳሳቱ ሐሳቦችና “ሃይማኖቶች” የሚጠፉ ሲሆኑ ክርስቶስ እውነተኛው ብርሃን፣ ክርስትናም እውነተኛ ሃይማኖት መሆኑን ተምረናል፡፡

# ይቀጥላል...

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org